የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ—ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 10
ADDIS ABABA - 24th Nov., 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፫/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፰፻፺፩

## CONTENTS

Proclamation No. 133/1998
Agency for the Administration of Rented Houses Establishment (Amendment) Proclamation ........................................ Page 891

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፫/፲፱፻፺፩
## የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፫/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር፶፱/፲፱፻፷፯ን ለማሻሻል ወጥቶ የነበረው አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፹፱ ተሽሮ የማቋቋሚያ አዋጁ እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

፩) አንቀጽ ፫ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፫ ተተክቷል፤

"፫· መቋቋም

፩) የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

## PROCLAMATION No. 133/1998
## A PROCLAMATION TO AMEND THE AGENCY FOR THE ADMINISTRATION OF RENTED HOUSES ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it is found necessary to amend the Agency for the Administration of Rented Houses Establishment Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Agency for the Administration of Rented Houses Establishment (Amendment) Proclamation No. 133/1998."

2. *Amendment*

Proclamation No. 311/1989 which was issued to amend the Agency for the Administration of Rented Houses Establishment Proclamation No. 59/1975 is hereby repealed and the Proclamation is re-amended as follows:

1) Article 3 is deleted and replaced by the following new Article 3:

"3. *Establishment*

1) There is hereby established the Agency for the Administration of Rented Houses (hereinafter "the Agency") as an autonomous federal agency having juridical personality.

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· የድርጅቱ ተጠሪነት ለሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ይሆናል ።"

፪· አንቀጽ ፯ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፯ ተተክቷል ፤

"፯· <u>የድርጅቱ አቋም</u>

ድርጅቱ፤

፩· አንድ የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ)

፪· አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፤ እና

፫· አስፈላጊ ሠራተኞች

ይኖሩታል፤"

፫· አንቀጽ ፰ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፰ ተተክቷል ፤

"፰· <u>የቦርድ አባላት</u>

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።"

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2) The Agency shall be accountable to the Ministry of Public works and Urban Development.''

2) Article 7 is deleted and replaced by he following New Article 7:

''7. *Organization*

The Agency shall have:

1) a Management Board (hereinafter ''the Board'');
2) a General Manager; and
3) the necessary staff.''

3) Article 8 is deleted and replaced by the following new Article 8:

''8. *Members of the Board*

Members of the Board including the chairperson shall be appointed by the Government; and their number shall be determined as may be necessary.''

3.. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 24th day of November, 1998.

Done at Addis Ababa, this 24th day of November, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE